| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ርእስ ፡ አንቀጽ ። |
| ርእስ ፤ | *"ያንድ ፡ ሰው ፡ ሽግግር ፦ የሽግግር ፡ ክስረት ፤ የክስረት ፡ ሽግግር"* |
| ደራሲ ፤ | *"ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ።* |
| ዕለት ፤ | *መጋቢ.ት* ፡ 2013 ፡ *ዓ.ም.* ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | *"ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው* ፥ ቍ.2013-004 |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ርእስ ፡ አንቀጽ ።

editorial | éditorial | اِفْتِتاحي

## ያንድ ፡ ሰው ፡ ሽግግር ፦
## የሽግግር ፡ ክስረት ፤
## የክስረት ፡ ሽግግር ።



ዛሬ ፥ መላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በኹለት ፡ የውንብድና ፡ ኀይሎች ፡ ጣምራ ፡ ጭቈና ፡ ሥር ፡ ትገኛለች ፦

- በሰሜናዊ ፡ ክፍሏ ፥ በባሕር ፡ ምድርና ፡ በደንከል ፡ ግዛቶቿ ፥ የ"ሻዕቢያ" ፡ የውንብድና ፡ አገዛዝ ፥ አለሕገ ፡ መንግሥትም ፡ ኾነ ፡ አለምርጫ ፥ የኢትዮጵያን ፡ ከፊል ፡ ሕዝብ ፡ ደፍጥጦ ፣ ከፊል ፡ ምድሯንም ፡ ዐንቆ ፡ ይዟል ፤
- በቀረው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክፍል ፥ የኢ..ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ቅሬታ ፡ ይዘት ፥ በባዕድ ፡ ሠራሹና ፡ በሕገ ፡ ወጡ ፡ *"ሕገ ፡ መንግሥት"* ፥ እሥልጣኑ ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፡ አላግባብ ፡ ተሰቅሎ ፥ ባንድ ፡ ወገን ፡ ፀረ ፡ ሀገር ፡ ዘመቻን ፡ ሲመራ ፥ በሌላ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፥ በሀገሪቱ ፡ ዕጣ ፡ ፈንታ ፡ ላይ ፡ ለዘለቄታው ፡ ሲውስንና ፡ ከባዕዳን ፡ ሲደራደር ፡ ይታያል ።

ኹለቱም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክፍሎች ፡ በሕዝብ ፡ ሰቈቃውና ፡ ጩኸት ፡ ተሞልተዋል ፤ ኹለት ፡ ዐምባ ፡ ገነኖች ፥ በፈረቃ ፥ አንዱ ፡ ነጂ ፣ ሌላው ፡ ተነጂ ፡ እየኾኑ ፥ በአስመራ ፡ እና ፡ በዐዲስ ፡ አበባ ፡ ጐዳናዎች ፡ መሽከርከርን ፡ አስለምደዋል ።

አሮጌው ፡ የአስመራው ፡ ዐምባ ፡ ገነን ፡ ኢሳይያስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፦ *"አክ!"* ፡ ብሎ ፡ አንቅሮ ፡ የተፋውን ፡ *"ምርጫ"* ፥ የዐዲስ ፡ አበባው ፡ ለማጅ ፡ ዐምባ ፡ ገነን ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድ ፡ ደግሞ ፥ የ*"ምርጫ"*ን ፡ ተስፋ ፡ እሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ እያለማ ፥ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ ግን ፡ የሀገር ፡ ፈረሳ ፡ ሴራውን ፡ ሲዶልት ፡ ዐድሮ ፡ ሲያስፈጽም ፡ ይውላል ፥ ሲሞዳሞድም ፡ ያመሻል ።

*"አሯሯጮች" ፡ ብሎ ፡ የተሣለቀባቸው ፣ ነፍሳቸውን ፡ የሼጡ ፡ "ፖለቲከኞች"ም ፥ ያች ፡ የፈረደባት ፡ ለምርጫ ፡* ተሳታፊዎች ፡ ፓርቲዎች ፡ እንድትከፋፈል ፡ ከምዕራቡ ፡ ዓለም ፡ የምትላክ ፡ የ 96 ፡ ሚልዮን ፡ ብር ፡ ድጐማ ፡ እንዳትቀርባቸው ፥ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ቍጭ ፡ ብለው ፡ ቊማሩን ፡ ተያይዘውታል ። *የነርሱ ፡ ሲገርመን ፥ አላግባብ ፡ ታስረዋል ፡ ብለን ፡ የምናከብራቸው ፡ የ"ፓርቲ" ፡ መሪዎች ፦ "ከእስር ፡ ተፈተን ፡ ከምርጫው ፡ ብንሳተፍ ፥ አኹንም ፡ ቢኾን ፡ እናሸንፋለን" ፡ ሲሉ ፡ በየዋህነት ፡ ለ"ምርጫ ፡ ቦርዱ" ፡ ዱልዱም ፡ አመራር ፡ የላኩት ፡ ምልጃ ፡ እጅጉን ፡ አስደምሞናል ። ለ"ፖለቲከኞች" ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ መልእክት ፡ አለን ፦ በኢ..ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ "ሕገ ፡ መንግሥት" ፡ መሠረት ፡ ከሚጠራ ፡ ምርጫ ፡ በመሳተፍና ፡ በ"ማሸነፍ" ፡ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ መቼም ፡ ቢኾን ፡ አይገኝም ፤ ውጤቱ ፡ ያው ፡ የሕዝብን ፡ እግዚእና ፡ የረመረመ ፡ ዳግም ፡ ዐምባ ፡ ገነንነት ፡ ይኾናል ። ወቅቱ ፥ የሕዝብ ፡ ሀገራዊ ፡ እግዚእና ፡ የሚረጋገጥበት ፡ የትግል ፡ ወቅት ፡ እንጂ ፥ የተገላቢጦሽ ፥ "የፖለቲካ ፡ ፓርቲዎች" ፡ ለጌትነት ፡ የሚሰትፉበት ፥ ሕዝብ ፡ ደግሞ ፡ ላሽከርነት ፡ የሚያደገድግበት ፡ አይደለም ። ትኽክለኛ ፡ ምርጫ ፡ የሚኖረው ፥ ሕዝብ ፡ ገዢነቱን ፡ ባስከበረበት ፡ ኹኔታ ፥ ራሱ ፡ ባጸደቀው ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ መሠረት ፥ "የፖለቲካ ፡ ፓርቲዎች"ን ፡ ለአሽከርነት ፡ ቅጥር ፡ ለማወዳደር ፡ ሲፈቅድ ፡ ብቻ ፡ ነው ።*

**የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ፥** ጧት ፡ ማታ ፦ *"ሕዝቦች"* ፡ እያለ ፡ የሚክድኽ ፥ በዚህ ፡ ባጥፌ ፡ ሕገ ፡ ውንብድና ፡ *መሠረትም ፦ "ከምርጫ ፡ ተሳትፌ ፡ እታደግኻለኹ"* ፡ ሲል ፡ የሚዋሽልኽ ፡ አላዋቂ ፡ *"ፖለቲከኛ"* ፥ በስሕተቱ ፡ ቢጸና ፥ ሕገ ፡ *መንግሥት* ፡ የመሥራት ፡ የእግዚእና ፡ መብትኽን ፡ እንደ ፡ ካደ ፡ ዐውቀኽ ፥ ተራኽን ፡ ይህን ፡ *"የሞኝ ፡ ፖለቲካ"* ፡ በመካድ ፥ እግዚእናኽን ፡ ለማስከበር ፣ ሕገ ፡ *መንግሥትኽን* ፡ ለመሥራትና ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ *መንግሥትኽን* ፡ ለመመሥረት ፥ ከጥንት ፡ በወረስከው ፡ ልማድኽ ፥ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፥ ከቀበሌ ፡ እስከ ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ በእየዕርከኑ ፡ *መሪዎችኽን* ፡ እየሠየምኽ ፡ ለትግል ፡ ቈርጠኽ ፡ በአንድነት ፡ ተነሥ ፣ ተደራጅ ፣ ታገል ❖

እግዚእናችንን ፡ የማስከበር ፥
ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥
ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡

ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ ለኢ..ሀ.ሥ.አ. ፡ እናብር!

የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

ሥልጡንሕዝብና ።
www.slttunhzb.net


©ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፥ 2013 ፡ ዓ.ም. ።